# ያፈጠጠው እውነት

ድንቁ ስማቸው

12-24-14

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ታህሳስ 4 ቀን 2007 ዓ.ም የወጣው የአንድነት ፓርቲው የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ከጋዜጠኛ ኃይለመስቀል አቻምየለህ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ነው፡፡ የፍኖተ ነፃነት ምክትል አዘጋጅ ኃይለመስቀል አቻምየለህን በተለያዩ የግል መጽሄቶችና ጋዜጦች በፋክት መጽሄትም ላይ በሚያወጣቸው ጠንካራ የፖለቲካ አስተያየቶች ከአንባብያን ጋር በስፋው መተዋወቁን ይገልፃል፡፡

ኃይለመስቀል አቻምየለህ በፋክት መጽሄት ላይ ሲፅፍ በነበሩት ጽሁፎች አስተያየት የመስጠትና ሀሳቡን በጽሁፍ የመግለጽ መብቱ የተጠበቀ ቢሆንም መፃፍ ጋዜጠኛ ያስብላል ካልተባለ በስተቀር ባህሪ ሀሳቡ ጋዜጠኛ ሳይሆን የፖለቲካ አክቲቪስት እንደሆነ በጽሁፎቹም አንባቢውን ወደራሱ የፖለቲካ እምነትና መስመር የመሳብ፣ የመግፋት፣ አመፅንና ሕዝባዊ እንቢተኝነትን ሲሰብክና ሲያስተምር የቆየ መሆኑን እርሱም አይክደውም፡፡

ጋዜጠኝነት ሚዛናዊነትን፣ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን በመርህ ደረጃ የያዘ የተለያዩ ወገኖችን ድምፅ በእኩልነትና ያለአድልዎ የሚያስተናግድ ከፍተኛ ኃላፊነትን ከተጠያቂነት ጋር አጣምሮ የያዘ ሙያ ነው፡፡ ይህን መሠረታዊ የሙያውን መርህ ኃይለመስቀል አቻምየለህ አንዲትም ቀን በየትኛውም መጣጥፉ አክብሮትም ሰርቶበትም አያውቅም፡፡ ለምኔስ ብሎ ያከብረዋል የእሱ ዓላማ ሌላ ነውና፡፡

የእነሱ ዓላማ በጋዜጠኝነት ስምና ሽፋን የፖለቲካ እምነቱን ማራመድና ማሰራጨት ብሎም ተከታዮችን ለማፍራት መትጋት እንጂ የጋዜጠኝነት መርህ ተከበረ አልተከበረ ለእሱና ለመሰሎቹ ደንታ የላቸውም፡፡ እነሱ የፖለቲካ እምነታቸውን በጋዜጣና መጽሄት አዘጋጅነት የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ የሚከውኑ አክቲቪስቶች እንጂ ጋዜጠኛም እንዳልሆኑ ነጋሪ ሳያስፈልጋቸው የራሳቸው ህሊና ያውቀዋል፡፡

በእርግጥም እሱ እንዳለው እሱና መሰሎቹም ሲገፉትና ሲያቀነቅኑት የነበረው በእነሱው አገላለፅ አብዮታዊ ጋዜጠኝነትን ነው፡፡ በዚህ ስም የሚጠራ ጋዜጠኝነት በጋዜጠኝነት ዓለም ወይንም በመዝገበ ቃላቱም ላይ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፤ አልተሰምቶም፡፡ ቀላል ፍቺው አብዮት ለማስነሳት የሚሰሩ ራሳቸውን በጋዜጠኝነት ስም የሰየሙ ሕዝብን ለሁከትና ለአመፅ ለእምቢታ የሚቀሰቅሱ ጋዜጣና መፅሄት በማሳተም ለዚሁ ሥራ የሚተጉ ሰዎች ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የፖለቲካ ድርጅት አክቲቪስትነት እንጂ መቼውኑም ጋዜጠኝነት ሊሆን አይችልም፤ ሆኖም አያውቅም፡፡

ከዚህ ሁሉ በግሉ ፕሬስም ሆነ በፕሬስ ነፃነት ስም ዋሻ ሰርቶ ከመሸሸግ ፖለቲካ ፓርቲው ሕጋዊነት ካለው ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት የእከሌ ፖለቲካ ፓርቲ ልሣን ብለው ለማሳተም አይከለክላቸውም፡፡ የተሰለፉለት የፖለቲካ ድርጅት በሀገር ውስጥ ሕጋዊነት ከሌለው የግድ በሽፋን በመንቀሳቀስ በግሉ ፕሬስ ስም ሲሰሩ የኖሩ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

ሌላው ማረጋገጫውም ሙሉነህ አያሌውና እሱ የፃፉት "የመለስ ውርስ" መፅሀፍ ሚዛናዊነት የሌለውና በጭፍን ጥላቻ የተሞላ በመሆኑ ግለሰቦቹ ጋዜጠኞች ሳይሆኑ የራሳቸውን የፖለቲካ መስመር አራማጅ የፖለቲካ አክቲቪስቶች መሆናቸውን ማረጋገጫ ነው፡፡ ሚዛናዊነትን ገድለው በጭፍን ጥላቻ የሚጋልቡ ፈረሶች መሆናቸውን ያሳያል፡፡ አሁን አፍጥጦ በራሳቸው አንደበት በዚህም ቃለ ምልልስ የተገለጠው ጉልህ እውነታ ይኼ ነው፡፡ ከትናንት እስከዛሬ የነበሩትን እውነቶች በማረጋገጫነት በአደባባይ የሚያሳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የግሉ ፕሬስ ቁልፍና መሠረታዊ ችግር ያለውም እዚሁ ላይ ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የፕሬሱን ሚና በተመለከተ ኃይለመስቀል ሸዋምየለህ ስለፕሬሱ ሚና የገለፃቸው በመሠረቱ የተቀባዥሩ ነጥቦችን አካቶ ይዟል፡፡

በአምባገነን ሥርዓት ውስጥ የሚኖር የፕሬስ ሚና እና የብሄር መንግሥት ግንባታን በጨረሱ አገራት መካከል የሚኖረው የፕሬሱ ሚና ለየቅል ነው ብሎ በምዕራባውያኑ ብያኔ ተሸብቦ አያውቅም፤ ተቋማት እንዲፈጠሩ መሥራት አልፎም ሥርዓታትን

እስከመቀየር የሚደርስ ተልዕኮ መሸከምን ጨምሮ ዴሞክራሲያዊ ሂደቶችን መርዳት ይሆናል በማለት ይገልፀዋል፡፡

ከፕሬሱ ሚና አንዱ ዴሞክራሲያዊ ሂደቶችን መርዳት የሚለው ትክክል ነው፤ ጋዜጠኝነት ወይንም ፕሬሱ አንድን የፖለቲካ ሥርዓት እስከመቀየር የሚደርስ ተልዕኮ ተሸክሞ ይሰራል የሚለውን ኅበዙ ከየት እንዳመጣው አይታወቅም፡፡

የኃይለመስቀል በሸዋምየለህ አገላለፅ በጋዜጠኝነትና በፕሬሱ ዓለም ተጠያቂነት ይዞ የመሥራት ተስፋውን ያቀጨጨውና የገደበው ይኸው ከሙያው እጅግ ያፈነገጠ ሙያውንም የገደለ ተስፋውንም ያጨለመው በግሉ ፕሬስና በግል ጋዜጠኝነት ስምና ሽፋን ተሰግስገው የራሳቸውን የፖለቲካ አጀንዳ ከግብ ለማድረስ ሥርዓት እስከመቀየር የሚደርስ ግልጽ ተልዕኮ አንግበው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ስመ ብዙ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንደነበሩና ዛሬም እንዳሉ የኃይለመስቀል በሸዋምየለህ ቀጥተኛ ገለፃ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

ቀድሞ የነበሩት ብዙዎቹ ሲከዱት ቢኖሩም ይኼ ጕበዝ ግን ሲሰሩበት የቆዩት የሚያራምዱት አብዮታዊ ጋዜጠኝነት እንደነበረ ሥርዓትን እስከመቀየር የዘለቀ ተልዕኮ መሸከማቸውን በአደባባይ አረጋግጧል፡፡ አንዱ ፕሬስ ሲዘጋ ሌላ በመክፈት ትግላቸውን መቀጠላቸውንም ከፍትህ ጋዜጣ እስከ ፋክት መፅሔት የነበረውን ጉዞ ገልፆታል፡፡

ጋዜጠኝነት ወይንም ፕሬሱ ለሥርዓት ለውጥ (መንግሥትን ለመለወጥ ለማውረድ ለመተካት) ይሰራል የሚል አንዲትም ዘለላ መስመር ከጥንት እስከ ዛሬ በሙያው መርህና ሥነ ምግባር ውስጥ የለም፤ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡

ጋዜጠኝነትም ሆነ ፕሬስ በእርግጥ በበቂ መረጃዎች፣ በተጨባጭ ሚዛናዊነትን ጠብቆ የሁለት ተቃራኒ ወገኖችን ሀሳብም ሆነ አስተያየት ለአንባቢው ያቀርባል፡፡ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶችን፣ የሕዝብ በደሎችን፣ የሙስና ችግሮችን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን፣ የፍትህ እጦትና መጓደልን፣ ምዝበራና ብኩንነትን ወዘተ…በምናባዊና በፈጠራ ዜናና መጣጥፍ ሳይሆን በተጨባጭ ያጋልጣል፤ ለሕዝብ ያሳያል፡፡ የችግር ብቻ ሳይሆን የመፍትሄውም አካል ሆኖ ሊታረሙና ሊሻሻሉ የሚችሉበትንም መንገድ ይጠቁማል፣ ያሳያል፡፡

ፕሬሱ መንግሥትም ሆኑ መሪዎች በተለያየ ደረጃ ያሉ ኃላፊዎች ግልፅነትና ተጠያቂነትን መርህ አድርገው እንዲሰሩ የታዩትን ስህተቶችና ደካማ ጎኖች እንዲያርሙና እንዲያስተካክሉ በሥልጣናቸው ያለአግባብ የሚባልጉትም ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በጋዜጠኛውም ሆነ በፕሬሱ በማስረጃ የተደገፉ ተጨባጭ ሥራዎች ተጠቃሚው ሕዝብም መንግሥትም ነው፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ጋዜጠኝነትም ሆነ ፕሬሱ ለሀገር ሠላም፣ ለሀገር እድገት፣ ለሕዝቦች አብሮነትና ተከባብሮ መኖር ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ የመፍታት ባህልን ለማሳደግ ይሰራል፡፡ ለሥርዓት ለውጥ የሚሰራው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲ ካድሬ አባላቱና የፕሮፖጋንዳ ሠራተኞቹ እንጂ ጋዜጠኛውና ፕሬሱ አይደለም፡፡

በእርግጥ በተለያዩ ሀገራት የግሉ ጋዜጠኛና ፕሬሱ በአብዛኛው የሚታወቀው ራሱን ሆኖ በመቆም ሳይሆን በገንዘብ ኃይል በመጠለፍ ሙያውንም አሽቀንጥሮ በመጣል የሌሎች መልዕክት ማስተላለፊያ ልሣንና አገልጋይ ሆኖ በመሥራት ነው፡፡ እነ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህም ዛሬ ራሱ በአደባባይ እንዳመነው ሲሰሩ የቆዩት በጋዜጠኝነትና በግሉ ፕሬስ ስም ተሸሽገውና ካባውን ለብሰው የራሳቸውን የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አጀንዳ በሕዝቡ ውስጥ ለማስረጽ ነበር፡፡

ይህም በፍቅር የሰከሩለትን በእነሱው አገላለጽ ሕዝባዊ አመፅና እምቢተኝነትን በጋዜጣና በመጽሄቶቻቸው ፕሮፓጋንዳ እየነዙ የሕዝቡን ልብ በማሸፈት አመጽ እንዲነሳ እናደርጋለን ብለው ሲሰሩ፣ ሲለፉ፣ ሲደክሙና ሲያልሙ ኖረዋል፡፡ ይህንን ነው አብዮታዊ ጋዜጠኝነት ብለው የሚጠሩት፡፡ ግለሰቡ ሕዝባዊ አመጽ አይቀሬ ነውም ብሏል፡፡ ለአንድ አብዮት መከሰት መሟላት ያለባቸው ገፊ ምክንያቶች የተሟሉ ናቸው ሲል ሌኒናዊ ትንተናዎችንም አቅርቧል፡፡

የ97ቱን ዓይነት መነቃቃት እንደሚጠበቅም ተናግሯል፡፡ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህም ሆነ ሙሉነህ አያሌው ተመስገን ደሣለኝ እያስፔድ ተስፋዬም ሆነ እስክንድር ነጋ ሌሎችም ምሁራን ተብለው የሚጠሩ የፕሮፓጋንዳ "ጠበብቶቹ" የቀለም አብዮትን በኢትዮጵያ ለማምጣት ከጀርባቸው በፋይናንስ በሚረዷቸው የውጪ ኃይሎች አጋዥነት፣ አማካይነትና አይዞህ ባይነት ተመልምለው ይህንኑ ሥርዓት የመለወጥ ተልዕኮ ይዘው ሲናውዙና ሲንከላወሱ የኖሩ ባተሌዎች ናቸው፡፡

ከሀገሪቱ ተጨባጭ እውነት የተፋቱ በከፋ ጭፍን ጥላቻ ተዘፍቀው ሲንዘፈዘፉ ሲንቀጠቀጡ ድንጋይ ሲነክሱ የኖሩና ያሉ ናቸው፡፡ በሥርዓት መቃወም ድምፅን ማስማት ሕጉን ተከትሎ መሄድ የሚጠቅመው ለሀገርም ለሕዝብም አብሮነትና ቀጣይነት መሆኑ እየታወቀ የምርጫ ሕጉንና ሥርዓቱን ተከትሎ መራመድ ውጤቱንም መጠበቅ ችግር ካለም በሕግ አግባብ መሄድ እየተቻለ ሁልጊዜም የሕዝብን አመፅና እምቢተኝነትን የመጨረሻው መፍትሄ ነው ብለው የሚያስቡ ኋላቀር ፖለቲከኞች ናቸው፡፡

ቀጣዩስ ምን ሊሆን ይችላል፣ ሀገሪቱስ ወደዬት ታመራለች ብለው በስክነት ማሰብ የተሳናቸው ወፈፌዎች ናቸው፡፡ የእነሱ ሥሌትም ሆነ ቀመር ኢትዮጵያን የከፋ ማጥ ውስጥ ከመክተት ባሻገር አንዳችም ምንም መፍትሄ ሊያመጡ አይችሉም፡፡ ይህ አክራሪ እጅግም ኋላ ቀር የሆነ በእልህና በጥላቻ የተመላ፣ በበቀል የተለወሰ ስሜታዊ አካሄዳቸው የት ያደርሰናል ተብሎ ሲታሰብ ለሀገርና ለሕዝብ የከፋ ውድቀትን እንጂ እድገትና ሠላምን አያመጣም፡፡

እነ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ የሚያቀነቅኑት የቀለም አብዮት ሕዝባዊ አመፅና እምቢተኝነት በቅርብ ዓመታት በርካታ ሀገራትን አፈራርሷቸዋል፡፡ ሕዝቡን ለእልቂትና ለሥደት ዳርጐታል፡፡ ሠላም ጠፍቶ ሰርቶ መግባት የሚናፈቅበት፣ የእለት ጉርስ የጠፋበት፣ ሥርዓት አልበኝነት የሰፈነበት፣ ኢኮኖሚያቸው የፈራረሰበት፣ ቅርሶቻቸው ከተሞቻቸው እንዳልነበሩ ሆነው የወደመበት፣ ብዙ ሺህዎች ያለቁበትን ታሪክ እኛም የዓለምም ሕዝብ በዓይኑ አይቷል፡፡

የእኛ ተቃዋሚዎችና አብዮታዊ ጋዜጠኞቻቸው ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚመኙት አጥብቀው የሚናፍቁት ይህንኑ መአት በኢትዮጵያ ውስጥ ተደግሞ ማየት ነው፡፡ እጅግ በጣም አሳፋሪ ሰዎች ናቸው፡፡ ገና የ2007ቱ ምርጫ ሳይጀመርና ውድድሩ ውስጥ ሳይገቡ ከወዲሁ መሸነፋቸውን አምነው ተቀብለዋል፡፡ ምክንያቱም ተወዳድረው ለማሸነፍ የሚያበቃቸው አንድም ምንም ምክንያት የለምና፡፡

ከወዲሁ በመጨረሻው የተሟጠጠ ሙት ብዕራቸው እየቀሰቀሱ ያሉት አመፅን ሲሆን ሕዝባዊ አመጹም አይቀሬ ነው ይሉናል፡፡ መሸነፋቸውን አምነው ተቀብለዋል፡፡ ኢሕአዴግን በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ ስለማይቻል ያለው መፍትሄ ሕዝባዊ

እምቢተኝት ነው ይላሉ፡፡ ሕዝቡ በአብላጫ ድምፅ ከመረጠው ሕዝባዊ እምቢተኝነት እንዴት ይመጣል ለሚለውም መልስ የላቸውም፡፡

ሕዝቡ በየትኛውም መስፈርት ለሁከትና ለአመፅ አይነሳሳም፡፡ የተቃዋሚውን ማንነት በተደጋጋሚ ያየና ጠንቅቆ የሚያውቀውም ስለሆነ በከንቱና በባዶ ፕሮፓጋንዳ አይታለልም፤ ልጆቹንም አይገብርም፡፡ ሠላሙን ሊያጣ አይፈልግም፡፡ ሥርዓተ አልበኝነት እንዲነግስ፣ ሀገሪቱም የጕሳ ብጥብጥና የአሸባሪዎች መፈንጪያ እንድትሆን በተዓምር አይፈቅድም፡፡ የሊቢያ፣ የሶሪያ፣ የግብፅ ወዘተ…ታሪክ በኢትዮጵያ አይደገምም፡፡

ይህን ዓይነቱን የከፋ ጥፋትና የሀገር ውድቀት የሚመኙ ቅጥረኛ ተቃዋሚዎች ሀገሪቱን ከባዕዳን ለሚያገኙት ዶላር ሲሉ የከፋ አዘቅት ውስጥ ለመክተት እንቅልፍ አጥተው ቢራወጡም አይሳካም፡፡

ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ በግሉ ፕሬስ ሚና የጋዜጠኝነት ሥራ የሚካሄድበት አለመሆኑን በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ከፍትሕ እስከ ፋክት በዋነኛነት የተቀነቀነው አብዮታዊ ጋዜጠኝነት ነው ብሎታል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ ሥራ መሆኑን አልሸሸገም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያን እየገዘገዘ ያለውን ስብስብ በሀገር ውስጥም በውጭም እየታገሉ ያሉ ኃይሎች አሉና ለዚያ አጠቃላይ የትግል ሂደት የድርሻን የማዋጫ ሥልት ነው ብሎታል፡፡ በእርግጥም ጋዜጠኝነትን ሳይሆን የፖለቲካ አክቲቪስትነት ሥራቸውን በግሉ ሚዲያ ስምና ሽፋን ሲወጡ ኖረዋል፡፡

በእኔ እምነት ይላል ኃይለመስቀል ቅድመ ምርጫ አሊያም ድህረ ምርጫውን ተከትሎ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ያሻል፡፡ ምርጫ ተኮር አምባገነኖች ምርጫ ውስጥ አመፅ ይጠብቃቸዋል፡፡ ያ መነቃቃት ደግሞ ወደ ሕዝባዊ አመጽ ያመራል፡፡ ይህ እውነት በምርጫው ሰሞን በአገራችን ተግባራዊ ይሆናል ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ ይህ ባይሆን እንኳን ሕዝባዊ አመፁን እኛ ማስነሳት ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ያላት ተስፋ ይን ብቻ ነውና ይላል፡፡ ለዚህም ነበር ሲሰሩ የኖሩት፡፡

ይህም ይታወቅ የነበረ በመሆኑ ምንም እንኳን ዛሬ በግልጽ የፖለቲካ መስመራቸውን ይዘው ቢወጡም አዲስ ነገር የለውም፡፡ ቀድሞውኑም ፕሮፓጋንዲስቶችና የፅንፈኛው አክራሪ ፖለቲካ መስመር አራማጆች እንጂ ጋዜጠኛ

እንዳልሆኑና እንዳልነበሩም ይታወቃል፡፡ ጋዜጠኝነቱን የተጠቀሙበት ለሽፋን የራሳቸውን ዓላማ ማራመጃ መሣሪያ በማድረግ ነውና፡፡

ሌላው አስገራሚው መልሱ ሀገሪቱን ወዴት ሊወስዷት እንዳሰቡ ሊገባ የሚችል ነገር የለም…ከፊታችን ከባድ መዓት አለ፡፡ ሕዝባዊ አመጽ በእርግጥም ይከሰታል፡፡ አብዮቱ ግብታዊ ከሆነ ግን ለሀገር ሕልውና አደጋ የሆኑ ሁለት የስህተት መስመሮች አሉ፡፡ የዘውግ ማንነትና ኃይማኖት…ሲል ይገልፃል፡፡

ሀገሪቱን ወዴት ሊወስዷት አሰቡ ለሚለው አባባሉ ከትናንት ወደ ተሻለ ልማትና እድገት ሥልጣኔ አበቋት፣ ስምዋንና ታሪኳን በአዲስ መልክ እንዲታደስ አደረጉ፣ ይህንን ያፈጠጠ እውነት ይህ በጭፍን ጥላቻ የተነከረ ሰው ሊያይና ሊመለከት አልቻለም፣ ቢያይም አያይምና፡፡ እነሱ ደካማ ጐንን እንጂ ብርቱ ጎንን ለማየት፣ ለመናገር፣ ለመመስከር ያልታደሉ በራሳቸው የቅዠት ዓለምና መነባንብ የሚኖሩ ነፍሣት ናቸው፡፡

መልካሙን መልካም ለማለት ሕሊናቸው አይፈቅድም፡፡ ከፊታችን ከባድ መዓት አለ ለሚለውም እነሱው ናቸው ከባድ መዓት ለማምጣት ሲያሴሩና ሲያደራጁ የኖሩት፡፡ የጥፋት ተልዕኮ ይዘው ለዚህች ሀገር መፍትሄው ሁሉ በእኛ እጅ ነው ሌላው አይመለከተውም አያገባውም የሚሉ ልዩነትና መቻቻልን የማይቀበሉ ጭፍኖች በመሆናቸው ሕዝብ አይሰማቸውም፣ አይቀበላቸውምም፡፡

ሕዝባዊ አመፅ እንዲከሰት ሲሰሩ ኖረው በእርግጥም ሕዝባዊ አመፅ ይከሰታል ሲል ለገለፀውም መልሱ ሕዝብ ከብርሀን ወደ ጨለማ የኋሊት መመለስን ስለማይፈቅድ አመፅን አያራምድም፡፡

ይህን ሲያቀነቅኑና ለዚህም ሲሰሩ የነበሩት ከፅንፈኛው የዲያስፖራ አክራሪ ተቃዋሚ ኃይል ጋር በፋይናንስና በምክር በትዕዛዝ እየተመሩ በሀገር ውስጥ የሚሰሩ ተቃዋሚዎች ሕዝባዊ አመፅ ለመቀስቀስ እየሞከሩ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ጥረታቸው ሁሉ በእርግጠኝነትም ይመክናል፡፡ የጥቂት ተላላኪዎች ጩኸትና አመፅ የሕዝብ አመፅ ተብሎ ሊጠራም አይችልም፣ እንቅስቃሴያችሁን ከጀመራችሁ ውሎ

አድሯል፡፡ እንደ ጤዛና ጉም በኖ ይጠፋል፤ ውርደታችሁንም በአደባባይ በሽንፈት ትቀበሉ ዘንድ ግድ ነው፡፡ በመሰሪዎች ሴራ ሀገርና ሕዝቧ አይጠፉም፡፡